| |
|---|
| 5ኛ ዓመት ቁጥር 2<br>5th Year No. 2 |

| |
|---|
| ሐረር ግንቦት 9 ቀን 1992<br>Harar May 17/2000 |

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONEL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሳጥን ቁጥር 272 |


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር 22/1992

የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 22/1992.......................................................................ገፅ 185


## አዋጅ ቁጥር 22/1992 የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ::

የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀፅ 26 ንኡስ አንቀፅ 2 (ሀ) መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል::

1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 22/ 1992 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2.ማሻሻያ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል::

1- በአዋጁ በተለያዩ በታዎች ላይ የሰፈረዉ «የሐረሪ ህዝብ ክልል» የሚለዉ አረፍተ ነገር «የሐረር ከተማ» በሚል ተቀይሯል::

2- በአዋጁ በተለያዩ በታዎች ላይ የሰፈረዉ « ሸንት ቤት» የሚለዉ ቃል « መጸዳጃ ቤት » በሚለዉ ተተክቷል::

3- ክፍል አንድ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 ተሰርዟል::

4- ክፍል አንድ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 26 ቀጥሎ የሚከተሉት ንዑስ አንቀፅ 27 እና 28 ተጨምሯል::

« 27. « የስልጣን ክልል » ማለት:- ባለስልጣኑ በሐረር ከተማና ከከተማዉ ክልል ዉጭ ሌሎች አግባብ ካላቸዉ አካላት የቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት የሚንቀሳቀስበት ክልል ማለት ነዉ:: »

«28. « የአገልግሎት ክልል » ማለት:- የሐረር ከተማ ማለት ነዉ::»

5- ክፍል 1 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ተሰርዟል::

6- ክፍል1 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዟል::

7- ክፍል 2 አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 6,7,8.9 ተሰርዟል::

8- ክፍል 3 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 1-ለ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል::

« አንድ ስራ አስኪያጅ ይኖረዋል::»

9- ክፍል 3 አንቀፅ 18 ስር ያሉ ንኡስ አንቀፆች ተሰርዘዉ በሚከተሉት ንዑስ አንቀጾች ተተክቷል::

1- የቦርዱ ተጠሪነት ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል::

2- የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን የክልሉ መንግስት በሚያወጣዉ ደንብ ይወሰናል::

3- የቦርዱ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ::

ሀ- የክልሉ ምክር ቤት ሊቀመንበር ................................ሰብሳቢ

ለ- የኢኮኖሚ ዘርፍ ኃላፊ ....... አባል

ሐ- የዉ/ል/ማ/ኢ/ቢሮ ኃላፊ ... አባል

መ- የሥ/ከ/ል/ቢሮ ኃላፊ ....... አባል

ሠ- የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም ................................ አባል

ረ- እንደ አስፈላጊነቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰይመዉ አንድ አባል ................................ አባል

ሰ- የባለስልጣኑ ስራ አስኪያጅ ... ፀሀፊ እና አባል

10- ክፍል 3 አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚከተለዉ መልኩ ተሻሽሏል::

«የባለስልጣኑን የስራ እቅድ መርምሮ ይወስናል፡ እንደ አስፈላጊነቱ ከክልሉ መንግስት ድጎማ በጀት ሲጠይቅ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል:: »

11- ክፍል 3 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1.2.3.4 ተሰርዘዋል::

12- ክፍል 5 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዘዋል::

13- ክፍል 5 አንቀፅ 33 በሚከተለዉ መልኩ ተሻሽሏል::

«አዋጅ ቁጥር 2/1988 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 6 በዚሀ አዋጅ ተሸሯል::

*ሐረር ግንቦት 9 ቀን 1992 ዓ.ም*

*ጋዛሊ መሐመድ*

*የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት*

*ፕሬዝዳንት*